# ፌደራል ትራንስፖርት ባለስልጣን

## የተሽከርካሪዎች የፍጥነት መገደቢያ መሳሪያ ስለመግጠም እና ስለማስተዳደር የወጣ መመሪያ

## ቁጥር 692/2013

ታህሳስ 2011

አዲስ አበባ

Generated by CamScanner from intsig.com

## መግቢያ

በዓለም ላይ እንዲሁም በሀገራችን የመንገድ ትራፊክ አደጋ አሳሳቢ እየሆነ መጥቷል። ለዚህም አደጋ ዋና መንስኤ የተሽከርካሪ ፍጥነት እንደሆነ የተለያዩ ጥናቶችና ምርምሮች ያሳያሉ። በዚሁ መሠረት የተሽከርካሪዎች የፍጥነት መገደቢያ መሣሪያ በመግጠም የተሽከርካሪዎች ፍጥነት በመገደብ አደጋውን መቀነስ ወሳኝ ነው። በመሆኑም ባለስልጣኑ በአዋጅ ቁጥር 468/1997 የተሰጡት ተግባራትና ኃላፊነቶች ውስጥ በአንቀጽ 7 ንኡስ አንቀጽ 3/ሐ/ የትራፊክ አመራሩ ውጤታማ የሚሆንበትን ስልት በመቀየስና ተግባራዊ ማድረግ እንዳለበት ከመደንገግና የትራፊክ አመራሩን ውጤታማ ለማድረግ በፍጥነት ምክንያት የሚደርሰውን አደጋ ለመቀነስ ባለስልጣኑ የመንገድ ትራንስፖርት ትራፊክን ለመቆጣጠር የወጣ የደንብ ቁጥር 208/2003 አንቀጽ 12 ንዑስ አንቀጽ 2 መሰረት ይህንን መመሪያ አውጥቷል።

## ክፍልአንድ

## ጠቅላላ ድንጋጌ

1. **አጭር ርዕስ**

   ይህ መመሪያ "የተሽከርካሪዎች የፍጥነት መገደቢያ መሣሪያ ስለመግጠም እና ስለማስተዳደር የወጣ መመሪያ ቁጥር 692/2013 ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

2. **ትርጓሜ**

   የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ መመሪያ ውስጥ፡-

   1. "ደንብ" ማለት የመንገድ ትራንስፖርት ትራፊክ መቆጣጠሪያ ደንብ ቁጥር 208/2003 እና ማሻሻያው ደንብ ቁጥር 395/2009 ነው።
   2. በደንቡ አንቀጽ 2 ስር የተሰጡ ሌሎች ትርጓሜዎች በዚህ ደንብም ተፈጻሚ ይሆናሉ።
   3. "ባለስልጣን" ማለት በፌዴራል ደረጃ ትራንስፖርት ለመምራት የተቋቋመው የትራንስፖርት ባለስልጣን ነው።
   4. "ትራንስፖርት ቢሮ" ማለት ትራንስፖርትን ለመምራት ስልጣን የተሰጠው የክልል ወይም የከተማ ትራንስፖርት ቢሮ ነው።



Generated by CamScanner from intsig.com

5. "የፍጥነት መገደቢያ መሣሪያ" ማለት በተሽከርካሪ ላይ የሚገጠመው የተቀናጀ የተሽከርካሪ ፍጥነት መቆጣጠሪያ መሳሪያ ከአለም አቀፍ ስርዓት አቅጣጫ (GPS) ጋር የተጣመረ ሆኖ እንደተሽከርካሪው ሁኔታ ወደ ሞተሩ የሚገባውን ነዳጅ ወይም አየር በመቀነስ የተሽከርካሪ ፍጥነት በህግ ከተደነገገ በላይ እንዳይፈጥን የሚቆጣጠር መሳሪያ ነው፣
6. "የሚመለከተው አካል" ማለት የፍጥነት መገደቢያ መሣሪያ በተሽከርካሪዎች ላይ እንዲገጠሙ የመፍቀድ ስልጣን ወይም ውክልና ያለው አካል ነው። "
7. "የፍጥነት መገደቢያ መሳሪያ አስመጪ" ማለት የፍጥነት መገደቢያ መሳሪያውን ከሚያመርተው ድርጅት ውክልና ማቅረብ የሚችል እና የፍጥነት መገደቢያ መሳሪያ የማስገባት የብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ ያለው ድርጅት ነው።
8. "መዳረሻ" ማለት ዕቃን ወይም ተሳፋሪን የጫነ ተሽከርካሪ ሊደርስ ወይም ሊያራግፍ የሚችልበት ቦታ ነው።
9. "ሰው" ማለት በተፈጥሮ ሰው የሆነ ወይም ህጋዊ ሰውነት የተሰጠው አካል ነው።
10. ማንኛውም በወንድ ፆታ የተደነገገው የሴትንም ይጨምራል።

3. ዓላማ

የዚህ መመሪያ ዓላማ በተሽከርካሪዎች ላይ የፍጥነት መገደቢያ መሣሪያ እንዲገጠም በማድረግ የተሽከርካሪ ፍጥነት የሚያስከትለውን የመንገድ ትራፊክ አደጋ መጠንና ጉዳት መከላከልና መቀነስ ነው።

4. የተፈፃሚነት ወሰን

ይህ መመሪያ በኢትዮጵያ ውስጥ ባለስልጣኑ በሚያወጣው የአፈፃፀም ቅደም ተከተል መሠረት በማንኛውም ተሽከርካሪ ላይ ተፈፃሚ ይሆናል።

## ክፍል ሁለት

## የተለያዩ አካላት ኃላፊነት

5. የባለስልጣኑ ኃላፊነት
    1. የፍጥነት መገደቢያ መሣሪያ ለሚያቀርበውና ለሚገጥመው አካል በወጣው መስፈርት መሰረት የብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ ይሰጣል፤ ያድሳል፤ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ይሰርዛል።
    2. የፍጥነት መገደቢያ መሣሪያን አጠቃላይ የቴክኒክ /ስፔስፊኬሽን/ ያወጣል።

Federal Democratic Republic of Ethiopia Ministry of Transport Transport Authority No. 1



Generated by CamScanner from intsig.com

3. የፍጥነት መገደቢያ መሳሪያ የተገጠመላቸው ተሽከርካሪዎችን የአሰራር ስርዓት በመዘርጋት ይቆጣጠራል፤ ይከታተላል።
4. ድንገተኛ የተሽከርካሪ ምርመራ በማድረግ የፍጥነት መገደቢያ መሳሪያው ስለመገጠሙ፣ በትክክል ስለ መስራቱ እና ባግባቡ ስለመታሸጉ ይከታተላል፤ ይቆጣጠራል፤ ይኽንን ባላሟሉ ተሽከርካሪዎች ላይ ህጋዊ እርምጃ ይወስዳል።
5. በዚህ መመሪያ የፍጥነት መገደቢያ መሳሪያ እንዲገጥም የተካተተ ማንኛውም ተሽከርካሪ የፍጥነት መገደቢያ መሣሪያ ያልተገጠመለት ከሆነ ዓመታዊ የተሽከርካሪ ማረጋገጫ ሰርተፍኬት እንዳያገኝ ያደርጋል፡
6. የተሽከርካሪ ፍጥነት መገደቢያ መሣሪያ የክትትልና የቁጥጥር ሥርዓቱ እንዲጠናከር ያደርጋል፤ የዕድሳት ጊዜውንም ይወስናል፡
7. የፍጥነት መገደቢያ መሣሪያውን በተመለከተ የአሰራር ማንዋል ያዘጋጃል።
8. ስለመመሪያው አተገባበር ለተለያዩ አካላት ግንዛቤ ይሰጣል፤
9. የፍጥነት መገደቢያ መሣሪያ የሚያቀርበዉና የሚገጥመው አካል የብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ ሲሰጥ ሊያሟላ የሚገባቸውን መስፈርት እና ህጋዊ የንግድ ፈቃድ ስለመኖሩ ያረጋግጣል።
10. የፍጥነት መገደቢያ መሣሪያው የሚገጠምላቸውን ተሽከርካሪዎች አይነት ቅደም ተከተል የአሰራር ስርዓት በማውጣት ተፈፃሚ እንዲሆን ያደርጋል።
11. የፍጥነት መቆጣጠሪያ መሳሪያ ለገጠመ ተሽከርካሪ ልዩ ምልክት ያዘጋጃል።
12. የመመሪያዉን ተግባራዊነት ይከታተላል፣ይቆጣጠራል፣ያረጋግጣል፤ መመሪያውን ተላልፈው በሚገኙ አካላት ላይ ተገቢውን አስተዳደራዊ እርምጃ ይወስዳል።
13. አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ በተሽከርካሪ የሚገጠመውን መሣሪያ በተዘጋጀው ስፔስፊኬሽን እና በተመረጠው ልዩ መለያ ( Brand name) መሰረት መሆኑን በሚመርጠው አካል ትክክለኛነቱን ማረጋገጥ ይችላል፤

6. የትራንስፖርት ቢሮ ኃላፊነት

1. የፍጥነት መገደቢያ መሣሪያ እንዲገጥም ግዴታ ያለበት ተሽከርካሪ መሳሪያውን ያልገጠመ እንደሆነ ዓመታዊ የተሽከርካሪ ማረጋገጫ ሰርተፊኬት እንዳያገኝ ያደርጋሉ።
2. የተሽከርካሪ ፍጥነት መገደቢያ መሣሪያ ስለመግጠም የወጣ መመሪያ ለማስፈፀም የክትትልና የቁጥጥር ሥራ ያከናውናሉ።



Federal Democratic Republic of Ethiopia Ministry of Transport Authority No. 1

Generated by CamScanner from intsig.com

ባለስልጣን ያስተላልፋሉ።

3. በክትትልና በቁጥጥር ያገኙትን መረጃ ለትራንስፖርት ባለስልጣን ያስተላልፋሉ።

## 7. የተሽከርካሪ ባለንብረት ኃላፊነት

1. ማንኛውም የተሽከርካሪ ባለንብረት ባለስልጣኑ በሚያወጣው ቅደም ተከተል መሠረት የፍጥነት መገደቢያ መሣሪያውን ህጋዊ ፈቃድ ካገኘ አካል ላይ በመግዛት በተሽከርካሪው ላይ ማስገጠም ይኖርበታል፤
2. ማንኛውም የተሽከርካሪ ባለንብረት የፍጥነት መገደቢያ መሣሪያው እንዲገጠም በመመሪያው የተካተተውን ተሽከርካሪ መሣሪያውን ሳይገጥም እንዲሽከረከር መፍቀድ የለበትም፤
3. የፍጥነት መገደቢያ መሳሪያ ትክክለኛውን አገልግሎት እየሰጠ መሆኑን የማረጋገጥ፤ የፍጥነት መገደቢያ መሳሪያ ትክክለኛውን አገልግሎት እየሰጠ መሆኑን የማረጋገጥ፤ ብልሽት ሲገጥመው እና ከአሽከርካሪው ሪፖርት ሲቀርብ እንዲስተካከል የማድረግ እና
4. የፍጥነት መገደቢያ መሳሪያው ሲበላሽ ለባለስልጣኑ ወይም ለትራንስፖርት ቢሮ የማሳወቅ ግዴታ አለበት።

## 8.የአሽከርካሪው ኃላፊነት

ማንኛውም አሽከርካሪ፡-

1. ባለስልጣኑ የፍጥነት መገደቢያ መሣሪያ እንዲገጠምለት በመመሪያው ላይ የተካተተው ተሽከርካሪ አይነት የፍጥነት መገደቢያ መሣሪያው ሳይገጠምለት ማሽከርከር የለበትም፤
2. የፍጥነት መገደቢያ መሣሪያው በትክክል የተገጠመ፣ ባግባቡ የታሸገ እና የሚሠራ መሆኑን ሳያረጋግጥ ማሽከርከር የለበትም፤
3. አሽከርካሪው የፍጥነት መቆጣጠሪያ መሣሪያው ብልሽት ሲያጋጥመው ለባለንብረቱ እና በአካባቢው ለሚገኘው ትራፊክ ተቆጣጣሪ በማሳወቅ በባለንብረቱ ወጪ በትራፊክ ተቆጣጣሪ ወይም በአካባቢው በሚገኝ የፀጥታ አካል በእጀባ እስከ መዳረሻው ድረስ ብቻ ማሽከርከር እና በመዳረሻ ቦታ ተሽከርካሪውን ማቆም አለበት፤

Federal Democratic Republic of Ethiopia Ministry of Transport Authority No. 1



Generated by CamScanner from intsig.com

## 9. የትራፊክ ተቆጣጣሪ ኃላፊነት

1. የተሽከርካሪውን ፍጥነት ሲጠራጠር እና ድንገተኛ ቁጥጥር በማድረግ ተሽከርካሪውን በማስቆም የፍጥነት መገደቢያ በአግባቡ የተገጠመ፤ ባግባቡ የታሸገ እና በትክክል የሚሠራ መሆኑን ያረጋግጣል፤
2. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ የትራፊክ ተቆጣጣሪው የፍጥነት መገደቢያ መሳሪያው ከተፈቀደው ፍጥነት በላይ የተስተካከለ ወይም አግባብነት በሌለው ሁኔታ መታሸጉን ሲጠራጠር ከሚመለከተው ትራንስፖርት ቢሮዎች ትክክለኛነቱን አረጋግጦ እስኪመጣ የአሽከርካሪ ብቃት ማረጋገጫ ፈቃዱን እስከ አምስት ቀን ይዞ ይቆያል።
3. በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ 2 መሰረት አሽከርካሪው በተቀመጠው ጊዜ ገደብ ውስጥ ከሚመለከተው ትራንስፖርት ቢሮ ማረጋገጫ ይዞ ካልመጣ የአሽከርካሪ ብቃት ማረጋገጫ ፈቃዱን ለወሰደበት ትራንስፖርት ቢሮ የተያዘበትን ምክንያት በመግለፅ ፈቃዱን ያስተላልፋል።

## 10. የተሽከርካሪ ምርመራ ተቋማት ኃላፊነት

ማንኛውም የተሽከርካሪ ዓመታዊ ምርመራ እንዲያከናውን ስልጣን የተሰጠው አካል፡-

1. የፍጥነት መገደቢያ መሣሪያው በሚመለከተው ተሽከርካሪ ላይ ስለመገጠሙ፣ በአግባቡ ስለመስራቱ እንዲሁም በአግባቡ ስለመታሸጉ ያረጋግጣል፤ ይህን ላላሟላ ተሽከርካሪ የተሽከርካሪ የብቃት ማረጋገጫ ሰርተፊኬት መስጠት የለበትም።
2. የፍጥነት መገደቢያ መሣሪያው ፈቃድ ከተሰጠው የንግድ ድርጅት ተገዝቶ የተገጠመ መሆኑን ማረጋገጥ አለበት፡

## 11. የፍጥነት መገደቢያ መሣሪያ አቅራቢ ኃላፊነት

ማንኛውም የፍጥነት መገደቢያ መሣሪያ የሚያቀርብ አካል፡-

1. የሚያቀርበው የፍጥነት መገደቢያ መሣሪያ ባለስልጣኑ የሚያወጣውን መስፈርት እና ደረጃ የሚሟላት፤
2. የብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ ከባለስልጣኑ የማግኘት፤
3. የፍጥነት መገደቢያ መሣሪያውን የመግጠም፣ የጥገናና እና እድሳት የማድረግ፤ እና ይህንን ለማከናወን ብቁ ባለሙያዎችን የመቅጠር፤



Generated by CamScanner from intsig.com

4. የፍጥነት መገደቢያ መሳሪያ የተገጠመላቸው ተሽከርካሪዎችን ብዛትና አይነት በተመለከተ በኤሌክትሮኒክስ እና በማኑዋል መረጃዎችን በማደራጀት በየወሩ መጨረሻ ለባለስልጣኑ የማሳወቅ፤
5. ለፍጥነት መገደቢያ መሣሪያው በቂ መለዋወጫ የማቅረብ፤
6. ባለስልጣኑ በሚያወጣው መስፈርት መሰረት የጥገናና እና የእድሳት አገልግሎት ለመስጠት የሚያስችለው የስራ ቦታ እና ባለሙያ የማዘጋጀት፤
7. የአለም አቀፍ አቅጣጫ(GPS) መቆጣሪያ ሰርቨር ሆነ ሌሎች አገልግሎቶች በሃገር ውስጥ ሆኖ የሚያገለግል መሳሪያ የማቅረብ፤
8. መሳሪያው ባለስልጣኑ ባወጣው መስፈርት መሰረት ደረጃውን የጠበቀ መሳሪያ ስለመሆኑ ባለስልጣኑ ከሚወክለው አካል የተረጋገጠ መለያ/ብራንድ/ ባቻ ለገበያ ማቅረብ አለበት።

ግዴታ አለበት።

## ክፍል ሶስት

## የተሽከርካሪ ፍጥነት መቆጣጠሪያ መሣሪያ እና የሚገጠምላቸው ተሽከርካሪዎች ፍጥነት እና ዓይነት

### 12. የተሽከርካሪ ፍጥነት መቆጣጠሪያ መሣሪያ

1. በተሽከርካሪ ላይ የሚገጠመው የተቀናጀ የተሽከርካሪ ፍጥነት መቆጣጠሪያ መሳሪያ ከአለም አቀፍ ስርዓት አቅጣጫ (GPS) ጋር የተጣመረ ሆኖ እንደተሽከርካሪው ሁኔታ ወደ ሞተሩ የሚገባውን ነዳጅ ወይም አየር በመቀነስ የተሽከርካሪ ፍጥነት በህግ ከተደነገገ በላይ እንዳይፈጥን የሚቆጣጠር መሳሪያ መሆን አለበት።
2. በተሽከርካሪ የሚገጠመው የፍጥነት መቆጣጠሪያ መሣሪያ የብቃት ማረጋገጫ ከተሰጣቸው የንግድ ተቋማት ብቻ የተገዛ፣ ደረጃው የተረጋገጠ እና የሚገጠም መሆን አለበት።
3. የፍጥነት መገደቢያ መሳሪያ ተገጥሞላቸው ወደ ሀገር ውስጥ የገቡ ተሽከርካሪዎች የተገጠመላቸው መሳሪያ ባለስልጣኑ ካወጣው መመሪያ እና እስታንዳርድ ጋር እንዲጣጣም ይደረጋል፤ ከመስፈርቱ ጋር ሊጣጣም የማይችል ከሆነ ተቀባይነት የለውም።



Federal Democratic Republic of Ethiopia Ministry of Transport Authority No. 1

Generated by CamScanner from intsig.com

4. በተሽከርካሪ የሚገጠመው መሣሪያ የብቃት ማረጋገጫ ከተሰጣቸው የንግድ ተቋማት ብቻ የተገዛ እና የሚገጠም ሲሆን ለዚህም መሳሪያው የአምራች መለያቁጥር ( manufactural Authorization Factory Certificate ) ያለው ሊሆንይገባል፤
5. መሳሪያው ከኔትወርክ ዉጪ (offline) ሆኖ የሚሰራ፤ ኔት ወርክ ሲያገኝ መረጃዎቹን ወደያውኑ የሚያስተላልፍ እና ተጨማሪ አገልግሎቶች እንዲሰጥ ሲታከልበት ከመረጃ ቋት (data base) ከያዘው ኮምፒዩተር ጋር በመረጃ መረብ ተገናኝቶ የሚናበብና መረጃ የሚያስተላለፍ መሆን አለበት።
6. የፍጥነት መቆጣጠሪያ መሳሪያው ተሽከርካሪው ከተወሰነለት ፍጥነት በታች ፍጥነቱን እንዲቀንስ በህግ በሚገደድበት ሁኔታዎች ሲኖር ተሽከርካሪው ከፊጠነ በድምጽ ወይም በምልክት ፍጥነቱን እንዲቀንስ ለአሽከርካሪ የሚያስጠነቅቅ እና ወደ መረጃ ማእከሉ መረጃ ማስተላለፍ የሚችል መሆን አለበት።
7. በዚህ መመሪያ መሰረት የፍጥነት መገደቢ መሳሪያ እንዲገጥም የተካተተ ተሽከርካሪ ቋሚ የመለያ ቁጥር ሰሌዳ ማግኘት የማይችልበት ሁኔታ ሲፈጠር እና በተላላፊ ወይም በዕለት ሰሌዳ በልዩ ሁኔታ ተሽከርካሪው ወደ ስራ ከተሰማራ የፍጥነት መገደቢያ መሳሪያውን ሳይገጥም መንቀሳቀስ የለበትም።

13. <u>የተሽከርካሪ የፍጥነት መጠን</u>

1. በተሽከርካሪዎች ላይ የሚገጠመው የፍጥነት መቆጣጠሪያ ጣሪያም የፍጥነት ወሰን ህጉ በሚደነግገው ከፍተኛ የፍጥነት ወሰን ጣሪያ መሠረት ይሆናል።
2. የዚህ አንቀፅ ንኡስ አንቀፅ 1 ቢኖርም አሽከርካሪው በትራፊክ መቆጣጣሪያ ደንብ መሠረት ፍጥነቱን ከተፈቀደለት የፍጥነት ወሰን በታች ማሽከርከር የሚገባው ሁኔታ ሲኖር ፍጥነቱን ቀንሶ ማሽከርከር ይገባዋል።

14. <u>የፍጥነት መገደቢያ መሣሪያ የሚገጠምላቸው ተሽከርካሪዎች</u>

1. የፍጥነት መገደቢያ መሣሪያ የሚገጠምላቸው ተሽከርካሪዎች የምርት ዘመናቸው እንደ አውሮፓውያን ዘመን አቆጣጠር ከ2000 እና በኋላ ያሉ ተሽከርካሪዎች ላይ ይሆናል።
2. በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ 1 የተደነገገው ቢኖርም በአንቀፁ ከተካተቱት ውጪ ያሉ ተሽከርካሪዎች ላይ የፍጥነት መገደቢያ መሳሪያው ስለሚገጠምበት ሁኔታ ባለስልጣኑ ወደፊት ይወስናል።



Federal Democratic Republic of Ethiopia Ministry of Transport Authority No. 1 የኢትዮጵያ ... በትራንስፖርት ...

Generated by CamScanner from intsig.com

3. ይህ መመሪያ ከፀደቀበት ቀን ጀምሮ ወደ ሀገር ውስጥ የሚገቡና በሀገር ውስጥ የሚመረቱ ተሽከርካሪዎች ባለስልጣኑ ፍቃድ ከሰጠው አካል የፍጥነት መገደቢያ መሳሪያ የተገጠመላቸዉ ብቻ ይሆናሉ።
4. የዚህን አንቀፅ አፈፃፀም በሚመለከት ባለስልጣኑ የአፈፃፀም ቅደም ተከተል በማውጣት ይወስናል።

## ክፍል አራት

## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

15. ስለተጠያቂነት

በዚህ መመሪያ ኃላፊነት የተጣለበት ማንኛውም ሰው መመሪያውን ተላልፎ ከተገኘ ባለስልጣኑ የሚወስደውን አስተዳደራዊ እርምጃዎች ጨምሮ አግባብነት ባለው ሕግ መሠረት ተጠያቂ ይሆናል።

16. ክልከላ

1. ማንኛውም የፍጥነት መገደቢያ መሣሪያ እንዲገጥም በመመሪያው ላይ የተካተተ ተሽከርካሪ መሣሪያዉን ሣይገጥም በመንገድ ላይ መንቀሣቀስ ክልክል ነው።
2. ማንኛውም ሰው ከሚመለከተው አካል የፍጥነት መገደቢያ መሳሪያውን ወደ ሀገር ውስጥ ለማስገባት ፈቃድ ሳያገኝ መሳሪያውን ማስገባትም ሆነ መግጠም ክልክል ነው።

17. የቅሬታ አቀራረብ ስነ ስርዓት

1. በዚህ መመሪያ አፈፃፀም ላይ ቅሬታ ያለው ማንኛውም ሰው ቅሬታው ከተፈጠረ ቀን አንስቶ በአምስት የስራ ቀናት ውስጥ ጉዳዩ ለሚመለከተው ለባለስልጣኑ ወይም ለሚመለከተው የትራንስፖርት ቢሮ ክፍል ማቅረብ ይችላል።
2. ቅሬታው የቀረበለት ክፍል ለቅሬታ አቅራቢው በአምስት የስራ ቀናት ውስጥ ምላሹን ማሳወቅ አለበት።
3. በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ 2 መሰረት በተሰጠው ውሳኔ ቅሬታ ያደረበት ሰው ቅሬታውን ቅሬታውን ለባለስልጣኑ ወይም ለሚመለከተው የትራንስፖርት ቢሮ የበላይ ኃላፊ ማቅረብ ይችላል።

18. አባሪ ሰነድ

ከዚህ መመሪያ አተገባበር ጋር በተያያዘ ባለስልጣኑ የሚያወጣቸው መስፈርቶች እና የሚያስተላልፋቸው የደብዳቤ ልውውጦች የዚህ መመሪያ አባሪ ሰነዶች ይሆናሉ።



Generated by CamScanner from intsig.com

19. ተፈጻሚነት የማይኖራቸው ሕጎች

የዚህን መመሪያ ድንጋጌ የሚቃረን ማንኛውም መመሪያ ወይም የአሰራር ልምድ ተፈጻሚነት አይኖረውም።

20. መመሪያውን ስለማሻሻል

አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ባለሥልጣኑ መመሪያውን ሊያሻሽለው ይችላል።

21. መመሪያው የሚፀናበት ጊዜ

ይህ መመሪያ ከ ----ሐምሌ 16---------- ቀን ----2011---------- ዓ.ም ጀምሮ የፀና ይሆናል።

Federal Democratic Republic of Ethiopia
Ministry of Transport Authority No. 1

አብዲሣ ያደታ ሙለታ
ዋና ዳይሬክተር



Generated by CamScanner from intsig.com